የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
Ethiopian Capital Market Authority

**ጥር 9 ቀን 2016 ዓ.ም**

# <u>ጋዜጣዊ መግለጫ</u>

**‘’የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016’’ ከዛሬ ጥር 9 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ ስራ ላይ ውሏል።**

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን "የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016" በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር መመዝገቡን እና በስራ ላይ መዋሉን በደስታ ይገልፃል።

ይህ መመሪያ ባለሥልጣኑ ከሚያወጣቸው መመሪያዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን የካፒታል ገበያ ተግባራት፣ ፈቃድ ለማውጣት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲሁም ፈቃድ የወሰዱ አገልግሎት ሰጪዎች የሚኖርባቸውን ኃላፊነት እና ግዴታዎች በመደንገግ በካፒታል ገበያ ውስጥ ላሉ አገልግሎት ሰጪዎች አጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ ሆኖ ያገለግላል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ብሩክ ታዬ እንደገለጹት “ይህ መመሪያ በሃገራችን የካፒታል ገበያን ለማስጀመር ወሳኝ ምዕራፍ ሲሆን ገበያው ተዓማኒ እና ፍትሐዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ እና የኢንቨስተሮችን ጥበቃ የሚያጎለብት የሕግ ማዕቀፍ ይሆናል።”

በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ 15 የተለያዩ የፈቃድ ዓይነቶች ይኖራሉ። እነዚህ ፈቃዶች የሚሰጡት በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ለሚያሟሉ አመልካቾች ሲሆን ባለሥልጣኑ እነዚህን አገልግሎት ሰጪዎች የሚቆጣጠር ይሆናል።

ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያን ለማስጀመር ዝግጅቱን እያጠናቀቀ ሲሆን ይህንንም ለማሳካት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል።

ለበለጠ መረጃ እና መመሪያውን ለማግኘት የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን ድረ-ገጽ (ecma.gov.et) ይጎብኙ።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን

ጥር 9፣ 2016

አዲስ አበባ